ጉባዔ ሰባት::

መሰንቆሁ ለዳዊት::

የዳዊት በገናው አንቺ ነሽ:: ዳዊት በበገናው ርኩስ መንፈስ ያወጣባታል፤ ድውይ ይፈውስባታል:: ይልቁንም ሳያልን ወየሐንቆ መንፈስ ርኩስ ይለዋል ርኩስ መንፈስ ይጥለው ነበር በገናውን ሲደረድርለት ይድን ነበር:: ምእመናንም የእመቤታችን ስሟን ሲጠሩ ከደዌ ይድኑባታል ከዲያብሎስ ፍላጻ ይጠበቁባታልና፤ ይህ ሁሉ መደረጉ ጌታ እመቤታችን በአብራኩ አሉና ለዳዊት የሃይማቱን ዋጋ የምታሰጪው አንቺ ነሽ፤ መሰንቆ ዘይቤ ሃይማኖት ይእቲ እንተ ለብስዋ ሰማዕት እንዲል::[68] ዳዊት ማለት ልበ አምላክ ማለት ነው፤ ጌታ የሚያደርገውን ሁሉ ተናግሯል፤ አንድም ጎሩይ ፍቁር ማለት ነው:: ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ይሁዳ ነው::

ወአክሊሉ ለሰሎሞን::

የሰሎሞን ትእምርተ መንግሥቱ ግርማ ሞገሱ አንቺ ነሽ:: አንድም ሐቲም ቀለበቱ አንቺ ነሽ:: ሰሎሞን ሐሩራኤል ጨርያቅ የሚባል ጎቡእ ስም በቀለበቱ ጽፎ ይዞ ይኖር ነበር:: ከሴት ሲገናኝ ተድላ ደስታ ሲያደርግ አንበሳ መደብ ሲወጣ ከዙፋኑ አድርጎት ይወጣል:: ከዕለታት አንድ ቀን ከዙፋኑ አድርጎት ወጣ ሰይጣን በእጁ እንዳይነካው ስመ

---

67 በጭንቅ ጊዜ ረድኤትን የምታፋጥኚ ማርያም ሆይ! እንደ ዐይን ጥቅሻ በላባ ቤት ያዕቆብን የረዳሽው አንቺ ነሽ፣በሁሉ ሐሳቢ በሁሉ ልቡናዋ አንቺን የማትወድ ነፍስ ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ:: ሰዓታት ዘእለ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

68 መሰንቆ ሰማዕታት የለበሷት ሃይማኖት ናት:: ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ

Scanned by CamScanner

እግዚአብሔር የተጻፈበት ነውና እንዳያታዥለው ፈርቶ ከነምንጣፉ ጠቅሎ ወስዶ ከባሕር ጣለው። ወቀለቦ ዓሣ ይላል የታዘዘ ዓሣ ተቀብሎ ዋጠው። ያም ሰይጣን ሄዶ ከዙፋኑ ላይ ተቀመጠ ሰሎሞን ተመልሼ እገባለሁ ቢል አጋፋሪው (ዘበኛው) ከለከለው፤ ተወኝ እኔ ሰሎሞን ነኝ አለው፤ ስንት ሰሎሞን አለ እሱስ ገብቶ ከዙፋኑ ተቀምጧል፤ ተመሰሰ ቀጣፊ አለው ሦስት ወር ከተማውን እየለመነ በልቷል። (ሦስት ቀንም ይላሉ) በምን ምክንያት ነው ቢሉ ድኃ ሲለምን አይቶ ይህ ምንድን ነው? አለ ድኃ ነው አሉት ምን እያለ ነው? ራበኝ ነው የሚለው አሉት። ረኃብ ምንድን ነው ብሎ ነበርና ምን ያድርግ የንጉሥ ልጅ በዕልፍኝ ተወልዶ በዕልፍኝ አደገ የነገሠው በዐሥራ ሁለት ዓመቱ በምን ይወቀው ይቅመሰው ብሎ ነው፤ ያም ሰይጣን የሰጡትን የሚበላ የሚጠጣ እየመሰለ የማይፈርድ የማይተች ሆነ ሄደው እጎቱም ሚስቱም ቢሉ አንድም ሳቤላ ለምትባል ነቢይት ሰሎሞን ልማድ ቀየረብን ባሕርይ ለወጠብን የማይፈርድ የማይተች ሆነብን ብለው ነገሯት። ሰሎሞን ምሁረ ኦሪት ነውና ዳግም ሕግን ከፊቱ ሆናችሁ እያበላሻችሁ አንብቡለት እሱ ከሆነ ይመልሳችኋል እሱ ካልሆነ አይመልሳችሁም በዚህ ታውቃላችሁ አለቻቸው። ካጠገቡ ሆነው ኦሪት ዘዳግምን እያበላሹ ቢያነቡ የማያርማቸው ሆነ፤ እሱ አለመሆኑን በዚህ አውቀዋል ጊዜ ይግለጠው ብለው ትተውታል፤ ከዕለታት አንድ ቀን ሰሎሞን ሲለምን ሰይጣን የሰውን ልቦና አጽንቶበት የሚሰጠው ሰው አጣ እስኪ ከዓሣ አስጋሪዎች ሄጄ ልለምን ብሎ ሄዶ ቢለምን ያን የሞተ ዓሣ አንሥተህ ውሰድ አለው። ተቀብሎ እበላለሁ ብሎ ሆዱን ቢቀደው ቀለበቱን አገኘት፤ ቀለበቴ ነሽ ከዚህ ማን አመጣሽ ብሎ ከጣቱ ቢያደርጋት ንጉሥ! ከዚህ መጥተዋል እያሉ ከበውታል፤ ያንንም ሰይጣን መርበብተ ሰሎሞን ደርሶ ወደ ህንድ አግዞታል። የሰሎሞን መግሥት በቀለበቱ እንደተመለሰችለት የሰው ክብሩ ጸጋው በእመቤታችን ተመልሶልናልና።

አንድም ሰሎሞን ፍርድ የሚያሰማበት ብይን የሚሰጥበት የክብር ዙፋኑ አንቺ ነሽ። ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ ሰሎሞን ከዝሆን ጥርስ ታላቅ ዙፋን አሠርቶ በወርቅ ዙርያውን አስለብጦ ወደ ዙፋኑ የሚያስወጡ ስድስት ስድስት እርከኖች አስደርጎ የዙፋኑን ራስ ክብ እንዲሆን አድርጎ በዙፋኑ ክንዶች መደገፊያ ላይ ሁለት አንበሶች

አስቀርያ በስድስቱም እርከኖች ላይ በቀኝና በግራ ሁለት አንበሶችን አቁሞ ታላቅ ዙፋን አሠርቷል። ይህ ምሳሌ ነው ዙፋኑ የእመቤታችን፤ ለሰሎሞን የጌታ ምሳሌ፤ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ ምሳሌ፤ ሰሎሞን ስድስቱን እርከን ወጥቶ ከዙፋኑ ተቀምጦ ሲፈርድ እንደሚውል ጌታም ከእመቤታችን ተወልዶ ዳኛ ላደላበት ፍርድ ለጎደለበት እውነተኛ ዳኛ ሆኖ ፍርድ የመስጠቱ ምሳሌ። አንድም በዚህ በወርቅ ዙፋን ላይ ከሰሎሞን በስተቀር ማንም እንደማይቀመጥበት አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ባደረበት በድንግል ማርያም ማኅፀን ፍጡር ዕሩቅ ብእሲ ያለማደሩ ምሳሌ። አንድም መኪንንቱና መሳፍንቱ በሰሎሞን ዙፋን ፊት ቆመው ምስጋና እንደሚያቀርቡ እመቤታችንም ጌታን ፀንሳ ሳለ ዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ማኅፀኗን ዓለም አድርገው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የማመሰገናቸው ምሳሌ። ኦ እግዝእትየ ማርያም ለሰሎሞን ዐራተ መንግሥቱ። አትሮንሱ ዘቀርነ ነጌ ወዘወርቀ ምዕራፍ መዝራዕቱ። ዘለኪ ይሰግዱ መላእክት ተስዓ ወተስዓቱ። ለኪ ይትቀነዩ ነገሥታት መታክፍቲሆሙ እንዘ ያቴሕቱ። እንዘ ይገንዩ ለክብርኪ ወዕበይኪ የአዙቱ እንዳለ ደራሲ።[69] ሰሎሞን ማለት መስተፋቅር መስተሳልም ማለት ነው። ዳዊትና ጌታ በታረቁበት ወራት ስለተወለደ ነው። ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ይሁዳ።

ገነት ዕጹት።

በውስጥ በአፍአ የታጠረች የተክል ቦታ አንቺ ነሽ። ይህንን የተክል ቦታ ሌባ እንዳይደርስበት እንስሳት እንዳይረግጡት በውስጥ በአፍአ ዙሪያውን ያጥሩታል። እመቤታችንም በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ በንጽሕና የታጠረች በቅድስና የተጠበቀች ስለሆነች የጎልዮ ጎጢአት የለባትም አጋንንት ድል አይነሧትምና፤ መንፈስ ቅዱስ አቀባ እምክርሠ እማ እንዲል። ገነት የእመቤታችን ምሳሌ፤ ተክል የጌታ አጥር የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።

ዐዘቅት ኅትምት።

በውስጥ በአፍአ የታተመች የተቆለፈች የውኃ ጉድጓድ አንቺ ነሽ። ይህንን የውኃ ጉድጓድ ጠላት መርዝ እንዳይነሰንስበት አራዊት

---

69 እመቤቱ ማርያም ሆይ ዘጠኙ ነገደ መላእክት የሚሰግዱልሽ፣ አትሮንሱ የዝሆን ቀንድና ክንዱም የወርቅ የሆነ የሰሎሞን የመንግሥቱ ዙፋን አንቺ ነሽ። ዝኒ ክማሁ ገጽ ፵፬

እንዲይተነፍስበት ለአምላ ለስድሳ የሚነሣ ጽኑዕ ደንቢያ ገጥመውት ይዟዳለ። ጠላት መርዝ እንዲነሰንስበት አራዊት እንዲይተነፍሱበት ጽኑዕ ድንጋይ እንዲገጥሙት በእመቤታችንም በድንጋሌ ሥጋ፣ በደንጋሌ ነፍስ፣ በደንጋሌ ጎሊና የጸናች ጎትምት ስለሆነች ልማደ አንስት ዘርአ ወራዙት የለባትም አጋንንት አይቀርቢትምና፣ የውኃ ጉድጓድ እንቺ ነሽ አለ።

መሰበ ወርቅ እንተ ኤልያስ።

የኤልያስ መሶበ ወርቅ እንቺ ነሽ በኤልያስ ጊዜ ንጉሡ አክዐብ ንግሥቲቱ ኤልዛቤል ይባላሉ፣ ለንጉሡ አራት መቶ ለንግሥቲቱ አራት መቶ ሃምሳ ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖት ነበሯቸው። ኃጢአት እየሠሩ ጣዖት እያመለኩ ተዉ ብሎ ቢመክራቸው የማይመለሱ ሆኑ፣ ይህ ሁሉ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ ቢመግባቸው አይደለም ከእንግዲህ ወዲህስ የፈጣሪያቸውን ማንነት የእነሱን ከንቱነት ይወቁት ሕያው እግዚአብሔር አምላክ ኀይል ዘቆምኩ ቅድሜክ ከመ ኢይረድ ዝናም ዘእንበለ በቃለ አፋየ ብሎ ሰማይንና ምድርን አወገዘ፣ ሰማይ ዝናም ለዘር ጠል ለመከር ከመስጠት፣ ምድርም የዘሩባትን ከማብቀል የተክሉባትን ከማጽደቅ ተከለከለች ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ይህን አድርጎ በክተማ ተቀምጦ ሳለ ኤልዛቤል ወይ እኔ ኖሬበት ወይ አንተ ኖረህበት ነው እንጂ መኳኵር አለን ብላ ላከችበት፣ መልአኩ መጥቶ ኤልያስ! ከነብር ትፋዘገር ዕንቅልፍ ታበገር እንዲሉ አክአብ ኤልዛቤልን ያህል ሰው ተጣልተህ፣ ዝም ብለህ ከዚህ ተቀምጠሃል? ተነሥተህ ሂድ አለው ተነሥቶ ሲሄድ ደከመው ወአዕረፈ ታሕተ ዕፀ ከርሜል ይላል ከደደሆ ዛፍ በታች ዐረፈ አንቀላፍቶት ተኛ፣ መልአኩ መጥቶ ቀስቅሶት ቢነሣ ከራስጌው ጎበስቱ በመሶበ ወርቅ ውኃው በመንቀል ተዘጋጅቶ አገኘው ያን ተመግቦ ተመልሶ ተኛ፣ ዳግመኛም ቀስቀሰው በልቶ ተኛ፣ ሦስተኛ ቀስቅሶ ተንሥእ ኤልያስ ወብላዕ እስመ ርኁቅ ፍኖትከ አለው ተነሥቶ ያን ተመግቦ ወሖረ በጽንዐ ውእቱ እክል አርብዓ መዐልተ ወአርብዓ ሌሊተ ምስለ ሰናብቲሃ[70] ይላል ያ የተመገበው ኀይል ጽንዕ ሆኖት አርባ ቀን ተጉዞ ገነት ገብቷል። ይህ ምሳሌ ነው መሶብ የእመቤታችን፣ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፣

[70] ያ ምግብ ኃይል ሆኖት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጣ። ፩ኛ ነገሥት ፲፱ ፰

ኅብስት የጌታ፣ አንድም ኅብስት የቅዱስ ሥጋው፣ ውኃው የክቡር ደሙ፣ ኤልያስ የምእመናን ምሳሌ፣ ኤልያስ ያ ምግብ ኀይል ጸንፅ ሆኖት አርባ ቀን ተጉዞ ገነት እንደገባ ዛሬም ምእመናን ሥጋውን በልተው ደሙን ጠጥተው ኀይል ሆኗቸው ገነት መንግሥት ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ። አንድም የደደሆ ዛፍ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ፣ ኤልያስ በዚች ዛፍ ተጠልሎ ከድካሙ እንዳረፈባት ምእምናንም በቤተ ክርስቲያን ተጠልለው ከድካመ ሥጋ ከድካመ ነፍስ ያርፉባታልና፤ በዚያች ኅብስትና ውኃ እንደ ተገኘባት በቤተ ክርስቲያንም ሥጋወ ደሙ ይፈተትባታል ስብሐተ እግዚአብሔር ይገኝባታልና። ኤልያስ ማለት ዘይት ማለት ነው፤ ወገደፈቶ ታሕተ አሐቲ ዕፀ ኤልያስ ወአሐቲ መስፈርተ ኤልያስ ታገምር አሠርተ ምክያዳተ ወይን እንዲል። ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ሌዊ።

መስክት ዘኤልሳዕ።

ልሕኵተ ኤልሳዕ አንቺ ነሽ፤ በኤልሳዕ ጊዜ ረኃብ ሆነ ደቂቀ ነቢያት ተሰብስበው ከኤልሳዕ ዘንድ ሄዱ ሄደውም ራበን አብላን አሉት ደቀ መዝሙሩን ግያዝን ጠርቶ ኅመን ቀቅለህ ስጣቸው አለው መጥፎውንና ጥሩውን ሳይለይ የሆነውን ያልሆነውን ሰብስቦ ቀቅሎ ሰጣቸው ቢቀምሱት መረራቸው፤ ሕምዝ ባቲ ልሕኵተ ኤልሳዕ ተባበሉ። እንዲህ ሲባባሉ በጸጋ አውቆባቸው የስንዴ ዱቄት አላትነህ ስጣቸው አለው፤ አላትኖ ቢሰጣቸው ምረቱ ጠፍቶላቸው ጣፍጧቸው ደስ ብሏቸው ተመግበዋል። ይህ ምሳሌ ነው ልሕኵት የእመቤታችን፣ ላተን የመለኮት፣ ምግብ የትስብእት፣ ምረቱ የፍዳ መርገም። ኤልሳዕ ማለት መልአክ አቃቤ ሀገር ማለት ነው፤ አንድም መድኅን ኖላዊ ማለት ነው፤ ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ይሳኮር።

ፅንስ ምስለ ድንግልና ዘኢሳይያስ።

ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት የተናገረልሽ አንቺ ነሽ። ኢሳይያስ ማለት መድኃኒት ቅቡዕ እምቅብዓ ትንቢት ማለት ነው፤ እናት አባቱ በትንቢቱ እንዲረባ እንዲጠቅም አውቀው አውጥውለታል። ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ስምዖን።

Scanned by CamScanner

ነቢዩ ዳንኤል ዕብን ዘተበትከ እምደብር ነዋኅ ዘእንበለ እድ ወይትቀባዕ ቅዱስ ቅዱሳን ወይትነተም ራእየ ነቢያት[71] ብሎ ትንቢት የተናገረልሽ ሰባዔ የቆጠረልሽ አንቺ ነሽ። ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ ነቢዩ ዳንኤልለጣዖት አልሰግድም በማለቱ ምክንያት በባቢሎን ከተራቡ አናብስት ጉድጓድ በግፍ ጣሉት መልአኩ መጥቶ የአናብስቱን አፍ ዘግቶለት እንደ ለማዳ ውሻ ሆነውለት ጠረኑን በማሽተት ብቻ ረኃባቸውን እያስታገሡ አጫውተውታል። ዳንኤል ጦሙን ውሎ አድሮ ስለነበር ዕንባቆም የተባለ ሰው ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በጎዳና በአምሳለ ጎልማሳ ሆኖ ተገናኝቶ አንተ ሰው! የያዝከውን ምሳ ወስደህ ለዳንኤል ስጠው አለው። አይቱ ሀሎ ለዳንኤል ወለባቢሎንኒ ኢየአምራ ዳንኤል ያለበትን ቦታ እኔ አላውቅም አለው ሌት በማንጠልጠያ በአንዲት ጣቷ የቅቤ ቅሏን እንደምትይዝ መልአኩ የዕንባቆምን አንዲት ጸጉሩን ይዞ ዳንኤል ካለበት ቦታ ወስዶ አደረሰው። ዕንባቆምም ጉድጓዱን ሳይከፍት እንደተቆለፈ ገብቶ መግቦት እንደተቆለፈ ወጥቷል። ዳንኤልም በምግብ ትንኝን የማይዘነጋ አምላክ እኔንም አልዘነጋኝም ብሎ አመስግኗል። ይህ ምሳሌ ነው ጉድጓድ የእመቤታችን፣ ዕንባቆም የጌታ፣ ዳንኤል የምእመናን ምሳሌ። ዕንባቆም ጉድጓዱን ሳይከፍት ገብቶ ዳንኤልን መግቦት ሳይከፍት እንደ ወጣ ጌታም ከእመቤታችን በጎቱም ድንግልና ተፀንሶ በጎቱም ድንግልና ተወልዶ ምእመናንን ሥጋ ወደሙን የመመገቡ ምሳሌ ነው። ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልድ ነገዱ ከነገደ ይሁዳ።

ወደብረ ፋራን ዘዕንባቆም።

ነቢዩ ዕንባቆም እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስሂ እምደብረ ፋራን ወእምአህጉረ ይሁዳ[72] ብሎ ትንቢት የተናገረልሽ ሰባዔ የቆጠረልሽ አንቺ ነሽ። ይህስ እንደምንድነው ቢሉ ዕንባቆም በዚች ተራራ አምስቱን ነገሥታት ድል ነሥቶባታል። ምእመናንም በእመቤታችን አጋንንትን ድል ይነሡባታልና። ደብረ ፋራን ማለት ነው ደብረ ጎይል ደብረ ጽንዕ ማለት ነው። ደብረ ጎይል ደብረ ጽንዕ

[71] እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስል እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየሁ። ዳንኤል ፪ ፥ ፴፬

[72] እግዚአብሔር ከቴማን ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ከይሁዳ አውራጃች ይመጣል። ዕንባቆም ፫ ፥ ፫

የተባለች የጎያል አምላክ ማደሪያ እመቤታችን ናት። ዕንባቆም ማለት ማእምር፣ ጠቢብ፣ ለባዊ ማለት ነው፤ ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ስምዖን።

ምሥራቅ ዕጹት ዘሕዝቅኤል።

ነቢዩ ሕዝቅኤል ርኢኩ ኖኅተ በምሥራቅ[73] ብሎ ትንቢት የተናገረልሽ ስባዔ የቆጠረልሽ ምሥራቅ አንቺ ነሽ። የቀድሞ ሰዎች ሲጸልዩ ፊታቸውን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አዙረው ነው፤ ወደ ቤተ መቅደስ የሚገቡትም በምዕራብ ነው። ስለምን ቢሉ ርደተ ገሃነም አለብን ሲሉ፤ እኛ ግን ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ የምንገባ ሆነናል፤ ርደተ ገሃነም የለብንም ስንል። በዚያ ልማድ ነቢዩ ሕዝቅኤል ፊቱን ወደ ምዕራብ መለስ አድርጎ ተቀምጦ ሳለ መልአኩ ኦ ወልደ እጓለ እመሕያው ተመየጥ መንገለ ከዋላከ ወደ ኋላህ ዘወር በል አለው ወሜጠኒ መንገለ አዜብ ይላል አዜብነቱ ለደብተራ ኦሪት ነው። ሕዝቅኤልም ፊቱን ወደ ምሥራቅ መለስ ቢያደርግ በምሥራቅ በኩል አዲስ አዳራሽ በአዲስ ቁልፍ ተቆልፋ ቁራዎች ዙሪያውን ከበዋት ቀይ ጎልማሳ ከአዳራሿ ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት ወጥቶ ቁራዎቹን በሰይፍ እያረደ ሲጥላቸው አይታል። ይህ ምሳሌ ነው፤ ቁራዎች የአጋንንት፣ ቀይ ገልማሳ የጌታ፣ ሰይፍ የሥልጣነ እግዚአብሔር፣ አዳራሽ የእመቤታችን፣ ቁልፍ የማኅተመ ድንግልናዋ ምሳሌ። ቀይ ጎልማሳ ከመቅደስ ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት ወጥቶ ቁራዎቹን እያራደ እንደ ጣላቸው ጌታም ከእመቤታችን በጎቱም ድንግልና ተፀንሶ በጎቱም ድንግልና ተወልዶ አጋንንትን በጎይሉ በሥልጣኑ በመስቀሉ ቀጥቅጦ የማስወገዱ ምሳሌ፤ ወአምላከ ሰላም ለይቀጥቅጦ ለሰይጣን በታሕተ እገሪክሙ ፍጡኖ[74] እንዲል። ሕዝቅኤል ማለት ጽኑዕ ጽንዐ እግዚአብሔር ማለት ነው፤ በጥሬው አዘቅ ማዘቅ ማለት ነው ያልተመለሰ ንባብ ነው፤ ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ሌዊ።

ወሙሳአ ሕግ ዘቤተ ልሔም።

የሕግ መውጫ የመሢሁ መገለጫ ቤተ ልሔም አንቺ ነሽ። አንድም የሕግ ክርስቶስ መገኛ ቤተ ልሔም አንቺ ነሽ። ሕግ ይወፅእ እምጽዮን

---

[73] ሕዝቅኤል ፵፬ ፥ ፩

[74] የሰላም አምላክ ሰይጣንን ፈጥኖ ከእግራችሁ በታች ይቀጠቅጠዋል። ሮሜ ፲፮ ፥ ፳

ወቃለ እግዚአብሔር አንሶስወት ወአስተርአየት ሕግ ውስተ ዓለም[75] እንዲል።

ወምድረ ኤፍራታ ዘሚክያስ።

ነቢዩ ሚክያስ ወአንቲኒ ቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ ኢትቤሐቲ እምነገሥተ ይሁዳ[76] ብሎ ትንቢት የተናገረልሽ ሰባዔ የቆጠረልሽ አንቺ ነሽ። ታሪክ እንደ ኀሙስ ውዳሴ ማርያም። ሚክያስ ማለት መነ ከማከ መሐሪ መነ ከማከ ልዑል ማለት ነው ትውልዳ ነገዱ ከነገደ ብንያም።

ዕፀ ሕይወት ዘሰሎንዲስ።

ሲሎንዲስ ሕመ.ማንን የሚያድንባት ደዌያትን ሁሉ የሚያርቅባት ዕፅ አንቺ ነሽ። ሲሎንዲስ ፈላስፋ ነው ሁለት ዕፀዋት አሉት በአንዱ ይገድልባታል በአንዱ ያድንባታል፤ እመቤታችንንስ በፈላስፋ እንጨት አይመስላትም ብሎ ምእመን ነው አምኖ ተጠምቆ ብዙ ሥራ ሠርቷል፤ ብዙ ድርሳን ደርሷል፤ ብዙ መጽሐፍ ጽፏል፤ ሊቃውንት በየድርሳናቸው ሲሎንዲስኒ ሰመያ ዕፀ ሕይወት ወዕፀ መድኃኒት ለእግዝእትነ ማርያም እያሉ ወስደውታል። አንድም ሲሎንዲስ ዕፀ ሕይወትን ዕፅ ዘየሐዩን ያውቅ ነበር፤ አንድም የተለያዩ ዕፀዋትን በጓሮው እየተከለ የታመመ ሰው ሲመጣ ደዌህ ምንድን ነው? ይለዋል። እንዲህ ነው ይለዋል፤ በል ሂድና እንዲህ ከሚባል ዛፍ ስር ተቀመጥ ይለዋል፤ ሄዶ ሲቀመጥ ይድናል፤ ሌላውም መጥቶ ደዌህ ምንድ ነው ይለዋል እንዲህ ነው ይለዋል በል ሂድና እንዲህ ከሚባል ዛፍ ቅጠሉን አሽትት ይለዋል ሄዶ ሲያሸት ይድናል፤ እንዲህ እያደረገ የተለያዩ ሕመ.ማንን በተለያዩ ዕፀዋቱ ይፈውስ ነበር፤ እመቤታችንም ምእመናንን በተለያየ ቃል ኪዳኗ በተለያየ ስመ አጠራሯ ምእመናንን ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ ፈውሳ እያስማረች ገነት መንግሥተ ሰማያት ታገባለችና። ሲሎንዲስ የሰሎሞን የፍልስፋና ስሙ ነው፤ ዕፀ ሕይወት ይእቲ ለእንተ ይትአመንዋ ወዕፀ መድኃኒት ለእንተ ይትመረጐዝዋ[77] እንዲል።

---

[75] የእግዚአብሔር ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔር ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣል። ሃይ. አበው ዘአትናቴዎስ ፳፱ ፥ ፲

[76] ትንቢተ ሚክያስ ፭ ፥ ፪

[77] እርስዋ ለሚይዙአት የሕይወት ዛፍ ናት፤ የተመረኮዘባትም ሁሉ ምስጉን ነው። ምሳሌ ፫ ፥ ፲፰

ወፈዋሲተ ሙስሉ ለናሆም።

ናሆም ከሙስለ ነነዌ የዳኑብሽ አንቺ ነሽ። አሁን ናሆም ቁስል ኑሮበት አይደለም ኦ ወለተ እስራኤል እፎ ኮኅሰ ጸልዕኪ. መአልበ ዘይፈውስኪ[78] ኢየሩሳሌም ሆይ በባቢሎን ቁስልሽን የሚፈውስ ስብራትሽን የሚጠግን ወዴት አለ እኔን ግን ጌታዬ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሰው ሆኖ ያድነኛል እያለ ይጸልይ ነበርና የድኅነተ ነፍስ ምልክቱ ድኅነተ ሥጋ እንደ ሆነ የሚጠተ ነፍስም ምልክቱ ሚጠተ ሥጋ ነውና። ሚጠተ ነፍስ በእመቤታችን ተደርጓልና ብሎ እንዲህ አለ። ናሆም ማለት ፈውስ፣ ፈዋሲ፣ ፈውሰ እግዚአብሔር ማለት ነው፤ ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ዛብሎን ነው።

ትፍሥሕት ዘዘካርያስ።

ነቢዩ ዘካርያስ አብርሂ አብርሂ ጽዮን ተፈሥሒ ፍሥሕት አ ወለተ ጽዮን እስመ ናሁ ንጉሥኪ በጽሐ እንዘ ይጼዓን ዲበ ዕድግት ወዲበ እዋለ ዓድግ[79] ብሎ ትንቢት የተናገረልሽ ሱባዔ የቆጠረልሽ አማናዊት ጽዮን አንቺ ነሽ። ዘካርያስ ማለት ዝኩር ዝክረ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ሌዊ።

ጽርሐ ንጽሕት ዘሚልክያስ።

ተፈሥሒ ቤተ እስራኤል ወተሐሠዪ ቤተ ይሁዳ ብሎ ነቢዩ ሚልክያስ ትንቢት የተናገረልሽ ሱባዔ የቆጠረልሽ አንቺ ነሽ። ሚልክያስ ማለት መልአክ፣ ሐዋርያ ማለት ነው ትውልዱ ነገዱ ከነገደ አሴር።

ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት ዘነቢያት።

ነቢያት በብዙ ጎብረ ትንቢት በብዙ ጎብረ አምሳል ትንቢት የተናገሩልሽ አንቺ ነሽ። ጎብረ ትንቢት ወነገርነሂ ከመ ሕፃን ወከመ ሥርው ጽምዕት ምድር ዘኢሳይያስ እስመ እምኔኪ ይወፅእ ንጉሥ ጽጌ አስተርአየ በውስተ ምድርነ፣ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ያለው ነው። ጎብረ አምሳል፤ በአምሳለ ሐመልማል ወነበልባል፣ በአምሳለ ዕብን ቅውም፣ በአምሳለ አንበሳ መፍርህ፣ በአምሳለ ብእሲ መካህ ያለው ነው።

---

78 ስብራትሽም አይፈወስም ቁስልሽም ክፉ ነው። ትንቢተ ናሆም ፫ ፥ ፲፱

79 አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በዪ እነሆ ንጉሥሽ ጸድቅና አዳኝ ትሁት ሆኖ በአህያና በአህያ ግልገል በውርንጫቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል። ዘካርያስ ፱ ፥ ፱

ምክሙ ለሐዋርያት።

የሐዋርያት ባለሟላችው አንቺ ነሽ። አንድም ባለሟል የምታደርጎያችው እመቤታችን በምን እንመስልሻለን፤ ጌታ ከእመቤታችን ባይወለድ ኖሮ ሐዋርያት፤ ሰባ አርድዕት እየተባሉ አይሾመም ነበርና። አንድም በማየ ገቦ ተጠምቀው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ከብረው ገነው ሕያዋን ሆነው ጸንተው ለዘለዓለም የሚኖሩበት ከእሷ ከተገኘ የተገኘ ነውና።

ኦሙ ለሰማዕታት።

የሰማእታት እናታቸው አንቺ ነሽ። አንድም የአደራ እናታቸው ሲል ነው፤ እኛን በዮሐንስ በኩል ለእመቤታችን፤ እመቤታችንን በዮሐንስ በኩል ለእኛ ሰጥቶናልና። ነዋ ወልድኪ ባለ ጊዜ ወነዋ ውሉድኪ ነያ እምከ ባለ ጊዜ ወነያ እምክሙ ሲለን ነው። እኛ በእውነት የዮሐንስን ሥራ ሠርተን ብንገኝ እመቤታችን ያደራ እናታችን ናትና። አንድም የሰማእታት መምህርታቸው አንቺ ነሽ። ሰማዕትነት እሳት ስለት ብቻ አይደለም ስደትም ሰማእትነት ነውና ስደትን ባርካ የሰጠቻቸው እሷ ናት፤ ሰማዕት ዘእንበለ ደም እንዲል።[80]

ወእኅቶሙ ለመላእክት።

የመላእክት እኅታቸው እመቤታችን! በምን እንመስልሻለን። እመቤታችን በቤተ መቅደስ ሳለች መላእክት ዐሥራ ሁለት ዓመት ዙሪያዋን ከበው እኅትነ ነያ እኅትነ ነያ እያሉ አመስግነዋታልና። አንድም በንጽሕና በቅድስና ትመስላቸዋለችና ዕገሌት ዕገሌን ትመስላለች እንደ ማለት።

ትምክሕቶሙ ለወራዙት ወደናግል ወመነኰሳት እለ ይተግሁ በውስተ አናቅጺሃ መዐልተ ወሌሊተ።

በመዐልትም በሌሊትም በየበሮቿ ተግተው ነቅተው ደጅ ለሚጠኑ ለወራዙት ለደናግል ለመነኰሳት መመኪያቸው አንቺ ነሽ። አንድም በበዓላቲሃ ይላል በየበዓሎቿ እንደ አክሱም እንደ ማሸን እንደ ጻድቃኔ ባሉ በዓላት ደጅ ለሚጠኑ ሁሉ መመኪያቸው አንቺ ነሽ። አንድም ዛሬ ልደታ ናት፤ ዛሬ በአታ ናት፤ ዛሬ ኪዳነ ምሕረት ናት፤ ዛሬ ቁስቋም ናት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ እያሉ በመዓልትና በሌሊት ደጅ ለሚጠኑ መመኪያቸው አንቺ ነሽ። አንድም በበመምህራኒሃ ይላል

[80] ሃይማኖተ አበው ዘአርሳርዮስ ዘአርማንያ ፲፫ ፥ ፩ ገጽ ፵፬

በየመምህራኑ ደጃፍ እየሄዱ ዛሬ ልደታ ናት፤ ዛሬ በአታ ናት፤ መቅድመ ተአምሯን አሰሙን እያሉ ደጅ ለሚጠኑ መመኪያቸው ሳንቲ ነሽ። አንድም ደናግል በድንግልና ታጸናናለች አስበ ድንግልናችንን ታስጠናለች ብለው፤ መከሳት በምንኩስና ታጸናናለች ምንኩስናችንን ታስፈጽመናለች ብለው፤ ወራዙት ዕድሜ ለንስሓ ዘመን ለፍሥሓ ታስጠናለች ብለው የሚመኩብሽ አንቺ ነሽ። አንድም ውስተ ሕዋሳቲሃ ይላል፤ በእንተ አጥባቲሃ እለ ሐፀናከ፤ ወበእንተ አዕዳዊሃ እለ ሐቀፋከ፤ ስላሳደጉህ ጡቶቿ ስለ አቀፉህ እጆቿ ብለህ ማረን ይቅር በለን እያሉ የተቀደሱ ሕዋሳቶችሽን አማላጅ አድርገው በመዓልትና በሌሊት ደጅ ለሚጠኑ መመኪያቸው አንቺ ነሽ። ወአንሣህልል ለኰናከ ኀበ መድረከ ኖኅት[81] እንዲል።

አ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተፀነስኪ።።

ድንግል ሆይ ወዘርእ ዘይወፅእ እምስካበ ተዐዳዌ ሕግ ይሰውን ለቅጥቃጤ ወለሐሣር[82] ባለው የተፀነስሽ የተወለድሽ አይደለም።።

አላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ።።

ክቡር አውስቦ በሱለሄ ወለምስካበሙኒ አልቦቱ ስዕበት[83] እንዲል ጋብቻ ክቡር ነው መኝታቸውም አደፍ ጉድፍ የሌለበት ንጹሕ ነው ባለው አምላካዊ ሕግ ከሐና ከኢያቄም ተፀነስሽ ተወለደሽ እንጂ።። አንድም ድንግል ሆይ እስመ ናሁ በኀጢአት ተፀነስኩ ወበዐመፃ ወለደተኒ እምየ[84] እንዲል በልተው ጠጥተው በሚያደርጉት ፍትወተ ሥጋ ተድላ ደስታ የተፀነሽ የተወለድሽ አይደለም።። አላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ።። አኮ ሠናይ ሰብእ ይንበር ባሕቲቶ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድኦ እንዲል[85] ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የምትመቸው ረዳት እንፍጠርለት ባለው መለኮታዊ ቃል መሠረት አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፤ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ተወስነው ከኖሩት ከሐና ከኢያቄም ተፀነሽ ተወለድሽ እንጂ።። ይህስ

---

81 አግሮችህን ወደ ቀምበሩ አግባ (አግረ ልቡናህና በስርዐቷ አጽና)። መጽሐፈ ሲራክ ፮ ፥ ፳፱

82 የአመንዝራ ልጆች ከቁጥር የጎደሉ ይሆናሉ። ሕግ ተላልፎ ከኃጢያት ምንጣፍ የተወለደ ልጅ ይጠፋል፤ አሳዋወራቸውም በዚህ በዓለም ምንም ቢበዛ ምንም ከመኖር አይቆጠርም ። መጽሐፈ ጥበብ ፫ ፥ ፲፮

83 መጋባት በሁሉ ክቡር ነው ለመኝታቸውም ርኩሰት የለውም። ዕብራውያን ፲፫ ፥ ፬

84 እነሆ በዐመፃ ተፀነስኩ እናቴም በኃጢያት ወለደችኝ። መዝሙር ፶ ፥ ፯

85 ዘፍጥረት ፪ ፥ ፲፰

Scanned by CamScanner

እንደምንድን ነው ቢሉ የእመቤታችን ቅድመ አያቶቿ ቂክታ በጥሪቃ ይባላሉ። ከወርቅ ከብር ከዕንቊ ከሴት ባሪያ ከወንድ ባሪያ ከፈረስ ከበቅሎ ከላም ከበሬ ከበግ ከፍየል ይህ ቀራችሁ የማይባሉ ባለጠጎች ነበሩ ነገር ግን ቂክታ መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም። ከዕለታት አንድ ቀን በጥሪቃ ከቤተ መዛግብቱ ገብቶ የገንዘቡን ብዛት የዕቃ ቤቱን ስፋት አይቶ ይህ ሁሉ ልጅ ቢኖረን ኖሮ ይወርሰው አልነበረም? ታዲያ ምን ይሆናል ልጅ የለንም ይህ ሁሉ ገንዘብ ለማን ይሆናል አላት። ቂክታም እግዚአብሔርት ከእኔ ባይሰጥህ ከሌላ ይሰጥህ ይሆናል ከሌላ ውለድ አለችው ይህንስ እንዳላደርገው እግዚአብሔር ያውቃል አላት፤ ወደ እግዚአብሔር እናመልክት አለችው። ወደ እግዚአብሔር በያመለክቱ እሷ ደግ ራእይ ታያለች ነጭ ዕንቦሳ ከበረታቸው ስትወጣ ዕንቦሳ ዕንቦሳይቱን፣ ዕንቦሳ ዕንቦሳይቱን፣ ስድስተኛይቱ ጨረቃን፣ ጨረቃ ፀሐይን ስትወልድ አየች። ይህን ትነግረዋለች በሀገራቸው መፈክረ ሕልም አለ ሄደህ አስፈታው አለችው። ሄዶ ቢነግረው ደጋግ ልጅ ልትወልዱ ይሆናል አለው። ጨረቃዩቱ ከፍጡራን በላይ የምትሆን ልጅ ትወልዳላችሁ፤ የፀሐይ ነገርስ አልተገለጠልኝም እንደ ነቢይ እንደ ንጉሥ ያለ ይሆናል ጊዜ ይግለጠው ብሎታል። ሲመለስ እንደምን ሆነህ መጣህ? አለችው። ደጋግ ልጅ ልትወልዱ ይሆናል አለኝ አላት፤ የፀሐይና የጨረቃስ ነገር? አለችው፤ ጨረቃ ከፍጡራን በላይ የምትሆን ልጅ ትወልዱ ይሆናል አለኝ የፀሐይን ነገርስ አልተገለጠልኝም ጊዜ ይግለጠው አለኝ አላት። ወናሁ ተዐቁረ እንል በውስተ ከርሥየ ይህንስ እኔም አውቀዋለሁ የፀሐይ ነገር ጊዜ ይግለጠው ብላለች ወዲያው ፀነሰች ሔሜንን ወለዱ፤ ሔሜን ማለት ረከብኩ ስእለትየ ማለት ነው። ሔሜን ዴርዲንን፣ ዴርዲ ቶናሕን፣ ቶናሕ ሲካርን፣ ሲካር ሔርሜላን፣ ሔርሜላ ሐናን ትወልዳለች። ሐና ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ኢያቄም የሚባል ደግ ሰው አግብታ ስትኖር እንደ አያቶቿ መካን ሆነች። ከዕለታት አንድ ቀን ልብስ አልደረሰልኝም እንጂ ከቤተ እግዚአብሔር ሄጄ እጅ ነሥቼ ጸሎት አድርሼ በመጣሁ ነበር አለች። አመንዝራ ጎረቤት ነበረቻትና፤ ሐና! ከእኔ ሁለት ልብስ አለ አንዱን ለብሰሽ ደርሰሽ አትመጪም አለቻት። ያንቺ ልብስ በአስበ ዝሙት የመጣ ነውና እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነው ንጹሕ ነገር ይወዳልና ያንን ለብሼስ ብለምነው አይሰማኝም ብዬ ነዋ አለቻት። ሐና!

Scanned by CamScanner

በምን ምክንያት ነው ለሐና ልጅ የነሣት እያልኩ አዝንልሽ ነበር ለካስ በዚህ ክፋትሽ ነው እንደ ዕንጨት አድርቀሽ እንደ በቅሎ አምክኖሽ ያስቀረሽ ይህች ቢወልዲት እንጂ የማትወልድ የበቅሎ ዘመድ ብላ ተሣለቀችባት። በዚህ አዝና ተክዛ የራሷን ለብሳ ከቤተ እግዚአብሔር እጅ ነሥታ ስትመለስ ርግቦች ከዛፍ ሥር ከልጆቻቸው ጋራ ሲጫወቱ አይታ አቤቱ ፈጣሪዬ ሁሉን ሁለት ሁለት አድርገህ ፈጥረኻዋል፤ ለመሆኑ ባሪያህ እኔን ምን ብለህ ፈጥረሃታል? ደንጊያ ብለህ ፈጥረሃታል? ለእንስሳቱ ለአዕዋፉ ያልነሣኸውን ዘር ለእኔ ለምን ነሣኸኝ ብላ ምርር ብላ አለቀሰች። ኢያቄምም ሮቤል የሚባል ጎረቤት ነበረው ኢያቄም! ምንስ እግዚአብሔር ባይቀበልልህም መባ አናቀርብም? ብሎ ተዘባብቶበታል። ይህ ብቻ አይደለም ከዕለታት አንድ ቀን ሐና ኢያቄም መሥዋዕት ይዘው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄዱ፤ ሊቀ ካህናቱ ስምዖን ምናሴም ይለዋል፤ ወኢይትቄከፍ መሥዋዕቶሙ ለመካናት እንጂ ይላል እናንተማ ብዝኑ ወተባዝኑ ብሎ ለአዳም የነገረውን ቃል ያስቀረባችሁ ርጉማን አይደላችሁምን ቢጠላችሁ ነው እንጂ ቢወዳችሁማ ልጅ ይሰጣችሁ አልነበረምን የኃጢአተኛውን መሥዋዕት እግዚአብሔር አይቀበለውም ምን አደከማችሁ አልቀበላችሁም ብሎ መለሰባቸው፤ በዚህ እያዘኑ ተመልሰዋል አንድም ከአዕሩገ እስራኤል የወለዱ ሰዎች የሚመገቡት፤ ያልወለዱ ሰዎች የማይመገቡት ተረፈ መሥዋዕት ነበር ያንን ነሥተዋቸው እያዘኑ ሲመለሱ ይህን ሁሉ ተግዳሮትና ስድብ የምንሰማው ወደ እግዚአብሔር ባናመለክት አይደለምን ብለው ሱባዔ ያዙ፤ ስእለት ተሳሉ፤ አቤቱ አምላካችን ሆይ ስድባችንን ብታርቅልን ልጅም ብትሰጠን፤ ወንድ ልጅ ከሆነ ወጥቶ ወርዶ አርሶ ቆፍሮ ያብላን ይርዳን አንልም፤ ለቤተ እግዚአብሔር መብራት አብሪ፤ መሥዋዕት አቅራቢ እንዲሆን ለአንተ እንሰጣለን። ሴት ብንወልድ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ እንጀራ ጋግራ ምግብ አብስላ ትርዳን ትጠብረን አንልም መሶበ ወርቅ ሰፍታ መጋረጃ ፈትላ እንድትኖር ለአንተ እንሰጣለን ብለው ብዕዐት ገቡ። የሐምሌ አመ ፴ ዕለት እሷ ለእሱ ጸምር ሲያስታጥቁህ መቋሚያህ አፍርታ ፍጥረት ሁሉ ከበው ሲመገባት አየሁ ብላ፤ እሱ ለእሷ ፀዓዳ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ መጥታ በራስሽ ላይ ስታርፍ፤ በቀኝ ጆሮሽ ገብታ በማኅፀንሽ ስታድር አየሁ ብሎ፤ ሁለቱም ያዩትን ራእይ

ተጨዋውተዋል። በሀገራቸው መፈክረ ሕልም አለና ሄደው ነገሩት ደግ
ልጅ ትወልዳላችሁ አላቸው አንተስ አልተረጎምከውም ጊዜ
ይተርጉመው ብለው ተመልሰዋል፤ ነሐሴ ሰባት ቀን መልአኩ መጥቶ
ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ ብሏቸው በብሥራተ መልአክ በፈቃደ አምላክ
እመቤታችን ተፀነሰች፤ በተፀነሰችም ጊዜ ብዙ ተአምራት ተደርጓል
የምትወዳት ምስጢሯን የምትነግራት በርሴባ የምትባል አንድ ዐይና
የሆነች አክስት ነበረቻት። ሐና! እግዚአብሔር በረድኤት ጎበኘሽ መሰለኝ
ጡትሽ ጠቆረ ከንፈርሽ ደረቀ መልክሽ አማረ ምናልባት ያ ያጫወትሽኝ
ነገር ተደርጎ ይሆን ብላ ሆዷን ብትዳስሰው ዐይኗን ብታሻው ዓይኗ ቦግ
ብሎ በርቶላታል። ይህን የሰሙ ሕመማኑ ሁሉ ሆዷን እየዳሰሱ
የሚፈወሱ ሆነዋል። ዳመኛም ሳምናስ ወልደ ጦሊቅ ዘይነብር በቤተ
ዶይቅ ይለዋል፤ ያጎቷ ልጅ ነው። ሞተ ብለው ነገሯት ሄዳ፤ ትወደው
ነበርና ቤተ ዘመድ ከሆኑ ያልጋውን ሽንኮር እየያዙ ማልቀስ ልማድ
ነውና እየዞረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ብድግ ብሎ ተነሥቶ፤ሰላም
ለኪ አ ሐና እማ ለፀሓየ ጽድቅ ወላዲቱ ወእምሕይወቱ ለዘንብረ ሰማየ
ወምድረ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የፀሓየ ጽድቅ እናትን የፀነሰሽ ሐና
ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን ብሎ ከመፈክረ ሕልም የተሠወረውን እሱ
ተርጉሞታል። ከዚያ የተሰበሰቡ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ቀድሞ
ከእነዚህ ወገን የተወለዱ እነዳዊት እነሰሎሞን አርባ አርባ ዘመን እንደ
ገል ቀጥቅጠው እንደ ሰም አቅልጠው ገዙን ደግሞ ዛሬ ከእነዚህ
የሚወለደው ደግሞ እንደምን ያደርገን ይሆን? ብለው ንዑ ንገሮሙ
በዕብን ወናውዕዮሙ በእሳት በድንጋይ ወግረን በእሳት አቃጥለን
እንግደላቸው ብለው በጠላትነት ተነሡባቸው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል
አድባረ ሊባኖስ ሂዱ ብሏቸው አድባረ ሊባኖስ ሄደው ወልደዋታል።
ትወጽእ መርዓት እምሊባኖስ[86] ያሰኛት አንዱ ይህ ነው። እመቤታችን
የተወለደች ዕለት ዓለሙ ሁሉ ብርሃን ሆኗል፤ ሐና ኢያቄምም ደስ
ብሏቸው ዳስ ሠርተው ፍሪዳ አርደው ጠጅ ጠጅተው ተድላ ደስታ
አድርገው ገንዘባቸውን ለነዳያን መጽውተዋል፤ የእመቤታችን ልደት
እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አይደለም ከጥንት ከመሠረት

---

[86] እንደ ማለዳ ብርሃን የበራሽ እንደ ጨረቃ የተዋበሽ ነውር ነቀፋ የሌለብሽ ርግቤ መደምደሚያዬ ንግሥታት የሚያወድሱሽ እኅቴ ሙሽራዬ ሆይ ልቤን በደስታና በሐሤት ደስ ታሰኝው ዘንድ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነዪ። መሓልየ መሓልይ ዘሰሎሞን ፬ ፥ ፰ ፤ ፮ ፥ ፰

በነቢያት አንደበት በብዙ ጎበረ ትንቢት ሲያያዝ ሲነገር የመጣ ነው እንጂ።

አ ድንግል አኮ በተላእኮ ዘልሕቲ ከመ አዋልደ ዕብራውያን አለ ያገዝፋ ኮማዶን።

ድንግል ሆይ አንቃዕቸውን እንደሚያሞጠሙጡ ደንደሳቸውን እንደሚያሳብጡ እንደ ዕብራውያን ሴቶች ልጆች በዋሣ በፈዛዛ በቢልት በጨዋታ ያደግሽ አይደለም። የዕብራውያን ሴቶች አታሞ ሲመቱ አንቃዕቸው ያብጣል እስክስታ ሲያወርዱ አንቃዕቸው ይቀጥናል።

አላ በቅድስና ወበንጽሕ ውስተ ቤተ መቅደስ ነበርኪ።

በቅድስና ወበንጽሕ ያለውን ይሻል፤ አንቺ ግን በቅድስና በንጽሕና በቤተ መቅደስ ጸንተሽ ኖርሽ እንጂ። አንድም ግዙፋነ ልብ እንደሚሆኑ እንደ ዕብራውያን ልጆች በቢልት በጨዋታ ያደግሽ አይደለሽም፤ በቤተ መቅደስ ያለውን ይሻል በቅድስና በንጽሕና በቤተ መቅደስ ጸንተሽ ኖርሽ እንጂ።

አ ድንግል አኮ ጎበስተ ምድራዊ ዘተሴሰይኪ።

ድንግል ሆይ ምድራዊ ጎበስትን የተመገብሽ አይደለም፤ አንድም የተመገብሽው ጎበስት ምድራዊ አይደለም።

አላ ጎበስተ ሰማያዊ እምሰማየ ሰማያት ዘበሰለ።

ከሰማይ የተገኘ ሰማያዊ ጎበስትን ተመገብሽ እንጂ። ዘበሰለ አለ በሰማይ ስንዴ አበዛ (ጋጋሪ) ምጎጎ (ምጣድ) ኖሮ አይደለም በሰማያዊ በመልአኩ እጅ ስለመጣ፤ በግብር አምላካዊ ከወደላይ መምጣቱን ሲያይ እንዲህ አለ እንጂ።

አ ድንግል አኮ ስቱ ምድራዊ ዘሰተይኪ።

ድንግል ሆይ ምድራዊ መጠጥን የጠጣሽ አይደለሽም፤ አንድም የጠጣሽው መጠጥ ምድራዊ አይደለም።

አላ ስቱ ሰማያዊ እምሰማየ ሰማያት ዘተቀድሐ።

ከሰማይ የተገኘ ሰማያዊ መጠጥን ጠጣሽ እንጂ። እምሰማየ ሰማያት ዘተቀድሐ ማለቱ በሰማይ ወይን ማድጋ አሳላፊ ኖሮ አይደለም በሰማያዊ በመልአኩ እጅ ስለመጣ፤ በግብር አምላካዊ ከወደላይ መምጣቱን ሲያይ እንዲህ አለ። አንድም ጎበስት ምድራዊና ስቱ

ምድራዊ፤ ዘተሴሰይኪና ዘሰተይኪ አንድ ወገን የወለድሽው በዘር በሩካቤ የተፈጠረ ዕሩቅ ብእሲ አይደለም። ዘበሰለና ዘተቀድሐ አንድ ወገን ነው ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደ አካላዊ ቃል ነው እንጂ። እመቤታችን የብዕዐት ልጅ ናት። ሦስት ዓመት ሲሆናት ሆዷ ሰው ሳይወድ አፉ እህል ሳይለምድ ወስደን አንሰጥምን የሰጠ ቢነሣ የለበት ወቀሳ እንዲሉ አንዳች ብትሆንብን ከልጃችንም ከእግዚአብሔርም ሳንሆን እንዳንቀር አለችው ኢያቄምም ፍቅርሽ ይለቅልሽ ብዬ ነው እንጂ እኔማ ፈቃዴ አይደለምን አላት ከፍቅሯ ጽናት የተነሣ ከጭኗ አውርዳት አታውቅም አንድ ቀን ብቻዋን አድርጋት ከደጅ ወጥታ ብትመለስ መልአኩ ሠውሮባት ጥራ ግራ አግኝታታለች፤ ከዚህ በኋላ ያው እየመሰላት ተለይታት አታውቅም። ወስደው ለቤተ እግዚአብሔር ሰጧት ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ይባላል አዕሩገ እስራኤልን ካህናቱን ሰብስቦ የምግቧን ነገር ሲማከር መልአኩ ቅዱስ ሩኑኤል ጎብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዞ ረቦ ታየ። ዘካርያስ ዛሬስ ማዕረጌን ክብሬን በሰው መሐል ሊገልጥልኝ ነው ብሎ ሊቀበል ቢነሣ መልአኩ ወደ ላይ ሰቀቀበት፤ አዕሩገ እስራኤልም ካህናቱም ሊቀበሉ ቢነሡ መልአኩ ወደ ላይ ሰቀቀባቸው፤ ሐናና ኢያቄምም ሊቀበሉ ቀረቡ መልአኩ ወደ ላይ ሰቀቀባቸው፤ ሐና! ጥበበ እግዚአብሔር አይመረመርምና ምናልባት ለዚች ብላቴና የመጣ ሀብት እንደ ሆነ እስኪ ትተሻት ጥቂት ዕልፍ በይ አሏት ትታት እልፍ ብትል ድንኩል ድንኩል እያለች እናቷን ስትከተል መልአኩ ፈጥኖ ወርዶ አንድ ክንፉን አጎናጽፎ አንድ ክንፉን ጋርዶ በቆመ ብእሲ ያህል ምድርን አስለቅቆ አቅፎ መግቧት አረገ። የምግቧ ነገር ከተያዘልን ከሰው ጋራ ምን ያጋፋታል፤ ኑሮዋ ከቤተ መቅደስ ይሁን ብለው ከቤተ መቅደስ አግብታው አኑረዋት ሄደዋል። መላእክት ከበው በዙሪያዋ ተከልክለው ዐሥራ ሁለት ዓመት አረጋግተዋታል። ከመዝ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ ወመላእክት ያመጽኡ ወትረ ሲሳየኪ ከመዝ ነበርኪ ዐሠርተ ወክልኤተ ዓመተ እንዘ ትትናዘዚ እምነበ መላእክት እንዲል።[87]

87 የተመረጥሽ ድንግል ሆይ! እንዲህ ሆነሽ በቤተ መቅደስ ውስጥ ኖርሽ፤ መላእክትም ዘወትር ምግብሽን ያመጡ ነበር፤ መላእክት እያረጋጉሽ እንዲህ አሥራ ሁለት ዓመት ኖርሽ፤ መጠጥሽም የሕይወት መጠጥ ነበር፤ ምግብሽም የሰማይ ጎበስት ነበር። አንቀጸ ብርሃን ዘቅዱስ ያሬድ

አ ድንግል አኮ ዘተአምሪ ርስሐተ ከመ አንስት አለ እምቅድሜከ. ወእምድኅሬከ።

ድንግል ሆይ ከአንቺ አስቀድሞ እንደነበሩ ከአንቺ በኋላም እንደሚኖሩ ሴቶች አደፍ ጉድፍ፤ የምታውቂ አይደለሽም፤ አንድም ልማደ አንስትን ርስሐተ ኃጢአትን ዘርአ ወራዙትን የምታውቂ አይደለም።

አላ በቅድስና ወበንጽሕ ሥርጉት አንቲ።

በቅድስና በንጽሕና ጸንተሽ ኖርሽ እንጂ፤ አንድም ንጽሕናን ቅድስናን ጌጥ ሽልማት አድርገሽ ኖርሽ እንጂ። መጀመሪያ ጐሥዐ ተናግሮ ነበርና ለዚያ አርእስት።

አ ድንግል አኮ ወራዙት ስፋጣን ዘናዘዙከ።

ድንግል! ተድላ ዓለም ብዕለ ዓለም የሸፈጣቸው አጋንንት በውዳሴ ከንቱ የሚያታልሏቸው ወራዙት ስፋጣን ቢል ሰውን በሎሚ በቀለበት የሚያታልሉ ወራዙት ያረጋጉሽ አይደለሽም። አንድም ሰፋጥያን ቢል ገሉን ጠጠሩን ወርቅ ብር አስመስለው በጨርቅ እየሰፉ ሴቶችን የሚያታልሉ ድል የተነሡ ወራዙት ያረጋጉሽ አይደለሽም። አንድም ፈቃደ ሥጋ ያታለላቸው ወራዙት ያረጋጉሽ አይደለሽም። ሰው በመቦል በመጠጥ ምክንያት ደም ሲመላ በፈቃደ ሥጋ ድል ይነሣልና።

አላ መላእክተ ሰማይ ሐወጹከ።

የሰማይ መላእክት ጎበኙሽ አረጋጉሽ አጫወቱሽ እንጂ።

በከመ ተብህለ ካህናት ወሊቃነ ካህናት ወደሱከ።

በነገረ ማርያም መላእክት ወሊቃነ መላእክት ወደሱ. ተብሎ እንደተነገረ ካህናትና የካህናት አለቆች አመሰገኑሽ እንጂ። ይህ እንደ ምንድን ነው ቢሉ መላእክት በቤተ መቅደስ ውስጥ ውድስት አንቲ ስብሕት አንቲ እያሉ ሲያመሰግኑ ሰምተው አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ዛሬስ የሐና የኢያቄም ልጅ ቤተ መቅደሳችንን የምትሐት ድምፅ ታሰማበት ጀመር ብለው በጠላትነት ተነሥተው በእሳት አቃጥለን እንግደላት ብለው ተሰብስበው ሄዱ። ቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ እሳት ሁኖ መላእክት በሐፀ እሳት በሰንተ እሳት እየነደፉ መልሰው ሰደዷቸው በሀገራቸው መጥቁል የሚባል አንድ መሠርይ አገኙ ወርቁን ብሩን ይዘው ላሙን ነድተው ይህ ለስር መማሻህ ላቅማዳ መፍቻህ ይሁን ዋናው ዋጋህን ኋላ እንሰጥሃለን የማንጋፋት እንዲህ ያለች ጠላት ተነሥታብናለችና እርሷን አጥፋልን አሉት ቆዩ እደሩ አላቸው

በበነጋው አጠፋታለሁ ብሎ በቀጠረበት ቀን ወርቁ ብሩ ገል ጠጠር ሆኖ፤ ልብሱን ብል በልቶት፤ እህሉን ነቀዝ በልቶት፤ ከብቱን ተኽር ፈጅቶት አደረ፤ ወይኔ መጥቁል! የሐና የኢያቄም ልጅ ሳልቀድማት ቀደመችኝ ብሎ ከበረሃ ወርዶ እጁን በጸፋ ሦስት መቶ ሰባ ሦስት አጋንንት ተሰብስበው ምን ብለኸን ነው? አሉት። እንዲህ ያለች ጠላት ተነሥታብኛለችና እሷን ታጠፉልኝ ብዬ ነው አላቸው፤ ወዳጃችን አንተማ ስትለን ምን የሚሳነን ነገር አለ፤ ለእመ ትብለነ አውርዱ ሰማየ ናወርድ ለከ ወለእመ ትብለነ ጠብልሉ ምድረ ንጠበልል ለከ ሰማዩን ጎትታችሁ አውርዱ ብትለን እናወርደዋለን፤ ምድሩንም እንደ ሸማ ጠቅልሉ ብትለን እንጠቀልለዋለን፤ የሚሳነን ነገር የለም። ወለእግዚአብሔርኒ ንኤዝዞ ከመ ገብር እግዚአብሔርን እንደ ባርያ እናዘዋለን፤ እንደ ገረድ እንልከዋለን ብለው አንድ ሰው ሠውቶላቸው ነበርና በልዑ ሥጋሁ ወሰትዩ መረቆ ሥጋውን በልተው ደሙን ጠጥተው ተማምለው መንገድ ጀመሩ። እመቤታችንም በጸጋ አውቃ ከነገረ ማርያም ሕርም ሰድክኤል የሚባል የእግዚአብሔር ጎበኤ ስም አለ ያን ብትደግምባቸው መልአኩ ወርዶ አጥፍቷቸዋል። እሱም ተማልቷቸው ሲአል ወርዷልና እንዲህ አለ። አንድም ምድር ተከፍታ ውጣቸዋለች። በዚህ ጊዜ ከአዳም ጀምሮ እስከ እርሷ ያሉት አበው በአማን ስብሕት አንቲ በአማን ውድስት አንቲ እያሉ አመስግነዋታልና እንዲህ አለ።